# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሣን *

ቅጽ 45፤ ቁ.1 ታህሣስ፤ 2009


## በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሰላም አይገዛም!

በተለያዩ ዘመናት አገራችን ኢትዮጵያ በሯን ጥርቅም አድርጋ ዘግታ ከዓለም ተለይታ የኖረችበት ዘመን ሲሰላ ከዓለም ሥልጣኔ ተቋዳሽ ሳትሆን ወደኋላ እንድትቀር ምክንያት ሆኗታል የሚል የታሪክ ዕውነታ ተመዝግቧል። ለምሳሌ በ8ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የአክሱም ሥልጣኔ መውደቂያና የዛጔ ሥርወ-መንግሥት መሸጋገሪያ ላይ፣ ለአምስት መቶ ዘመን ያህል ከዓለም ተለይታ በሯን ዘግታ የኖረችበትን ዘመን የታሪክ ፀሐፊዎች የጨለማው ዘመን ብለው ይጠሩታል። ከዚያም በኋላ አፄ ሱስንዮስን ከሥልጣን አስወግደው ዙፋኑን የወረሱት ልጃቸው አፄ ፋሲል፣ በአገራችን ውስጥ ለካቶሊክ ሃይማኖት መስፋፋት ምክንያት የሆኑት የውጭ አገር ሰዎች ስለሆኑ ከእንግዲህ አንድም የውጭ ዜጋ በአገሬ መሬት ላይ እንዳላይ በማለት ጠራርገው ከኢትዮጵያ በማስወጣታቸው፣ አገራችን ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር ለብዙ ዓመታት ሳትገናኝ ኖራለች። በእነዚህ ሁለት የታሪክ ዘመናት ውስጥ በዓለም ላይ ብዙ ኅብረተሰብን የሚጠቅሙ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶች ቢፈጠሩም፣ አገራችን የዓለም ኅብረተሰብ ያገኘውን የሳይንስና የማኅበራዊ ኑሮ ውጤቶች ሳታገኝ መቅረቷ የማያጠራጥር ዕውነታ ነው።

ዓለም በሥልጣኔ መጥቃ ወደፊት በምትገሰግስበት በአሁኑ ወቅት አምባገነኑ የህወሓት አገዛዝ ያለሕዝብ ፈቃድ በጉልበት ጨምድዶ የያዘውን ሥልጣንና በሙስና ያግበሰበሰውን ገንዘብ ላለማጣት ሲል፣ በአገራችን ለስድስት ወር የሚዘልቅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል። በተለያዩ የዴሞክራሲ አገሮች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚወጣውና የሚደነገገው የገገሩን መደብ ለመጥቀም ተብሎ ሳይሆን ሕዝብና አገር በተፈጥሮ አደጋ ሲጠቃ፣ የውጭ ኃይሎች ጣልቃገብነት ሲኖርና ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ ሕዝብና መንግሥት ተደጋግፈው አገሪቱን እንዲታደጉ ለማድረግ ነው። አምባገነኖች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጁት ግን ማናቸውንም እርምጃዎች በመውሰድ

ሕዝቡን እንደፈለጉ ለመግደል፣ ለማሰር፣ ለመርገጥና በሥልጣን እንዲቆዩ ለማድረግ እንዲያመቻቸው ነው። በሀገራችን የታወጀው ጊዜያዊ አዋጅ ዋና ዓላማውም መብቱን በሰላማዊ መንገድ የጠየቀውን ሰፊ ሕዝብ ጨለማን ተገን አድርጎ እስካሁን እየፈጸም ያለውን አፈናና ግድያ በከፋ ሁኔታ ለመቀጠልና ለኢ-ሰብዓዊ ድርጊቱን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ነው።

አገዛዙ ከታሪክ ለመማር የማይፈልግ በመሆኑ እንጂ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ የአንድ መንግሥት ሥልጣን ፀንቶ እንደማይቆም የሙባረክ መንግሥት በሕዝብ ማዕበል እንደተናደ ተመልክቶ ትምህርት በሆነው ነበር። እንዲሁም ግብፅ ከእስራኤል ጋር ጦርነት ከገጠመችበት ጊዜ ጀምሮ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየች ብትሆም አዋጁ አንዋር ሳዳትን ከሞት እንዳላዳነው በተገነዘበም ነበር።

በአገራችን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ አገዛዙ በራሱ አንደበት እንዳቀረበው 11 ሺህ ሰዎችን ማሰሩን ገልጿል። ይሁንና ቁጥሩ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል የህወሓት የፀጥታ ኃይሎች ቀን በቀን በኦሮሚያ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በኮንሶና በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች በየጎዳናው የሚገድሉትና ቤት ለቤት እየዞሩ የሚያፍሱትን ሕዝብ ግምት ውስጥ ስናስገባ ቁጥሩ እጅግ በርካታ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም። የግፉ ግፍ የእስረኞች ቤተሰቦች ስንቅ እንኳን እንዳያቀብሉ እስረኞችን ከአካባቢያቸው አርቀው በማሰራቸው፣ ቤተሰቦቻቸውን ለበለጠ ችግር ዳርጓቸዋል። ጎጃምና ጎንደር የተያዙ እስረኞችን ጋምቤላ ወስዶ ማሰር ምን ይባላል?

ይህ ኢ-ሰብአዊና አምባገነናዊ እርምጃ ትግሉን ከሰላማዊ አመፅ ወደ ትጥቅ ትግል እንደቀየረውና ለህወሓት የእግር እሳት እንደሆነበት በተጨባጭ እያየነው ነው። አገዛዙ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በኦሮምኛ ተናጋሪዎችና በሌሎችም አካባቢዎች ሕዝቡ በሰላማዊ መንገድ የመብት ጥያቄ እንዳያነሳ፣ እንዳይናገር እንዳይጽፍ፣ ከቶውንም ከሁለት ሰው በላይ ቆሞ ማውራት እንኳን እንዳይችል ባወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከተማዎችን በልዩ የወታደር ኃይል አጥሮ በመያዙ ሕዝባዊ ትግሉን ከዳር ለማድረስ ቆርጦ የተነሳው ወጣት ከታጋይ አርሶአደሮች ጋር በመቀላቀል ትግሉን በትጥቅ ቀጥሏል። የሕዝብ ወገን የሆነው ወታደርም እየከዳ የሕዝቡን ትግል እየተቀላቀለ ነው።

የውጭ ግንኙነት በመቋረጡ የህወሓት አገዛዝ ከኢንተርኔትና ከአገር ጎብኝዎች የሚያገኘው ገቢ ተሟጦ ለኪሳራ መዳረጉንም የራሱ የቱሪዝም ሚኒስተሩና የኮሚኒኬሺን ኃላፊ የነበረው

ጌታቸው ረዳ ሊደብቀው ያልቻለው ሃቅ ነው። የውጭ ሀገር ኤምባሲዎች ከአገሮቻቸው ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በመቋረጡ ከፍተኛ ቅሬታ እያሰሙ ነው። የአገዛዙ የገንዘብ ደጓሚ አገሮችም "ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር" እንደሚባለው፣ ስላፈሩበት የወሰዳችሁት አቋም ተቀባይነት የለውምና አስቡበት እያሉ በመጎትጎት ላይ ናቸው። በዚህ አዋጅ ምክንያት መንግሥት ተብዬው ከሕዝብ ጋር ያለው ጥላቻ እጅግ በተባባሰ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል። ልጁን ከቤቱ እየገቡ እያፈኑ ሲወስዱበት፣ ደጃፉ ላይ ሲገሉበት፣ እንደ አውሬ እያደኑ በዱላ እየቀጠቀጡ አካለ ጎደሎ ሲያደርጉበት የማያዝንና ቂም የማይዝ ወላጅ ይኖር ይሆን? እንኳንስ ወላጅና ባዕድም ከፍተኛ ቁጭት ያድርበታል እንጂ ህወሓትን ጥሩ አደረግህ የሚል አይገኝም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህወሓትን እንደማይፈልግ በምርጫ 97 በማያጠራጥር ሁኔታ አሳይቷል። አገዛዙ ግን በጠብመንጃው አማካኝነት በግድ እገዛችኋለሁ በማለት የሥልጣን ባለቤት ሆኗል። በአሁኑ ጊዜ ግን እንደቀድሞው አስገድዶ ለመግዛት ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ይኸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብሎ ማውጣቱ ራሱ ምስክር ነው። አዋጁን በመጠቀም በከተማዎች አካባቢ በእያንዳንዱ ሰው ደጃፍ ወታደር በማቆም ሰላም የሰፈነ ለማስመሰል ቢሞክርም ሕዝቡ ከአገዛዙ ጋር አለመሆኑን በተለያየ መንገድ እየገለጸ ነው። ህወሓት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ የሕዝቡን አንደበት ሰጥ ለጥ አድርጎ የሚገዛ መስሎት ነበር ይሁን እንጂ በኢኮኖሚ፣ በሶሻል፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ ዘርፎች በራሱ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ አድርሷል። ከዚህ ከገባበት አዘቅት ለመውጣት መውጫ ቀዳዳው ጠፍቶት እየተጨነቀ መሆኑንም ጠቅላይ ምኒስቴር ተብዬው በቅርቡ ለአሻንጉሊቱ ፓርላማ ያሰማውን ንግግር በማዳመጥ ማረጋገጥ ይቻላል።

የህወሓት አገዛዝ የትግሉን ግለት ያበረደ መስሎት አንዱን ሙሰኛ አንስቶ በሌላ ሙሰኛ በመተካት ለውጥ እያደረግን ነው በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብና የዲፕሎማሲውን ዓለም ለማታለል እየሞከረ ነው። "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" እንዲሉ፣ አንድን በሕዝብ የተጠላ ገዳይ አንስቶ በሌላ ገዳይ መተካት የሕዝብን ጥያቄ ከቶውንም አይመልስም። ትናንት በደቡብ ኢትዮጵያ አማርኛ ተናጋሪዎችን ተወልደው ካደጉበት መኖሪያቸው እያሳደደ የጨፈጨፈውንና በሺህ የሚቆጠሩት በበረሃ ተጥለው የአውሬ እራት እንዲሆኑ ያደረገውን ፀረ-ሕዝቡን ሺፈራው ሽጉጤን በሚኒስቴር ደረጃ ማስቀመጥ፣ ደግ አደረግህ በማለት ሽልማት ማበርከት እንጂ ሙስናን ወይም ወንጀለኛነትን መዋጋት አይደለም። የአገዛዙን መጥፎ ገጽታ ከቶም ሊለውጠውም አይችልም። እንዲያውም የህወሓት አገዛዝ ለሕዝብ ያለውን ንቀት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ድርጊት ነው። በተቃራኒውም የህወሓት

ጭቆናና የግፍ አገዛዝ አንገፍግፎት በቁርጠኝነት የተነሳውን የሕዝብ ቁጣ ይበልጥ እንዲጠናከር አደረገው እንጂ ከቶውንም አላዳከመውም።

የሕዝብን መነሳሳት የተመለከቱ ቀቢፀ-ተስፈኞች ሥልጣን በእጃቸው የገባ መስሏቸው፣ ከህወሓት አስተሳሰብ በባሰ ሁኔታ ኢትዮጵያ ካልፈረሰች የእኛ ምኞት አይሳካም የሚሉ ጭፍን ጠባብ ብሄረተኞች ብቅ ብቅ በማለት ላይ ናቸው። ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ አደጋዎችን ተቋቁማ ከዚህ የደረሰችው ለዘመናት ተሳስሮ በኖረው በዜጎቿ አንድነትና ኅብረት በመሆኑ የአሁኑም ትውልድ እንደ አያቶቹና ቅድመ አያቶቹ በአንድነት ቆሞ ታሪክ ለመሥራት እንደ እሳተገሞራ እየተፍለቀለቀና እንደነበልባል እየተንቦገቦገ ህወሓትን እንደሚለበልበውና ሀገራችን ከገጠማት ጊዜያዊ ችግር በአቸናፊነት እንደምትወጣ ኢሕአፓ (አንድነት) ለአፍታም ያህል አይጠራጠርም። በመሆኑም በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የመብት ማስከበር ትግልም ሙሉ በሙሉ ይደገፋል። ገና ከምሥረታው ጀምሮ ብሄረሰቦች ሁሉ መብታቸው ተከብሮ በዴሞክራሲዊት ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም አብረው መኖር ይችላሉ የሚል ጽኑ እምነት ያለው በመሆኑ ከዚህ እምነቱ ተፃራሪ የሆነውን ከፋፋይና ፀረ-ሕዝብ አቋም ለመመከት በትግራይ፣ በጎንደርና በጎጃም የበርካታ አባላቱን ሕይወት በመሰዋት ህወሓትን ተፋልሟል። ጭቆና የደረሰበትን ሰፊ ሕዝብ የዴሞክራሲዊ መብቱን ማስከበር የሚቻለው ተነጣጥለን በመቆምና ቂም በቀል በማስተማር ሳይሆን በጋራ በመታገል ብቻ ነው እንላለን።

ኢሕአፓ (አንድነት) ቀጥለው ለተዘረዘሩት የሕዝብ ጥያቄዎች አገዛዙ በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ በጥብቅ ይጠይቃል።

1ኛ. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲነሳ፣

2ኛ. የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ምክንያት የታሰሩ የወልቃይት/ጠገዴ የሕዝብ ተወካዮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣

3ኛ. በሰላም ሠርተው የሚኖሩ ዜጎችን በጎንደር፣ በጎጃም፣ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች፣ በኮንሶና በሌሎችም የአገራችን ክፍሎች ያለ በቂ ምክንያት ከሰላማዊ ኑሯቸው እያፈነ እሥር ቤት የተወረወሩ ዜጎች ያለምንም ቅደመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲለቀቁ፣

4ኛ. በፖለቲካ ልዩነታቸው ምክንያት ብቻ ያለፍርድ እሥር ቤት የሚንገላቱ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባሎች፣ ጋዜጠኞችና፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ሁሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንዲሁም፣

5ኛ. በኦሮሚያ፣ በኮንሶ፣ በጎጃምና በጎንደር ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ቤተሰቦች ሁሉ ካሳ እንዲከፈል አጠንክረን እንጠይቃለን።

ተቃዋሚ ኃይሎችም ልዩነታችንን አቻችለን በአንድነት ቆመን በመንገዳገድ ላይ ያለውን አምባገነኑን አገዛዝ በማስወገድ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት ሊኖሩ የሚችሉባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንድንመሠርት ደጋግመን እንዳስገነዘብነው እነሆ ዛሬም ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያን አንድነት በትግላችን ይከበራል!